# የ 2009 ዓም 11ኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ቀን በዓል በካናዳ በሚገኙት በኦታዋ እና በቶሮንቶ ከተሞች ተከበረ



በኦታዋ የተገኙ የበዓሉ ታዳሚዎች በከፊል፣



በቶሮንቶ የተገኙ የበዓሉ ታዳሚዎች በከፊል፣

**ክብርት አምባሳደር ብርቱካን አያኖ በካናዳ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ልዩ መልዕክተኛና ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር**

**ለበዓሉ ታዳሚዎች ንግግር ሲያደርጉ**



**በአታዋ**



**ቶሮንቶ**

ክብርት አምባሳደር ብርቱካን አያኖ ባደረጉት ንግግር የዘንድሮውን በዓል ልዩ የሚያደርገው ባሳለፍነው ዓመት በአገራችን ተከስቶ የነበረው ሁከት በህዝባችን ተሳትፎ ተወግዶ መንግስትም ጥልቅ የተሀድሶ እርምጃ መውሰድ በጀመረበት ወቅት የሚከበር መሆኑ እንደሆነ ጠቅሰው ይህ የተሀድሶ እርምጃ የተሳካ እንዲሆን እና የአገራችን ህዳሴ እንዲቀጥል ዳያስፖራችን በውስጡ ያሉ ጥቂት ድንፈኞችን  በጽናት መታገል ጨምሮ አገራችን እያካሄደች ላለው የልማት፣ የዴሞክራሲና የሰላም ጥረቶች የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረጉን እንዲቀጥል ጥሪ አድርገዋል። ከዚህ ጋር በማያያዝም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ-መንግስት የአገራችን ብሔር ብሔረሰቦች ለዘመናት ተነፍገው የነበሩትን ሁለንተናዊ እኩልነታቸውን ያጐናፀፋቸው በመሆኑ እንደ ዐይን ብሌናቸው እንደሚጠብቁት ገልፀው በካናዳ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያንም በአገር ቤት ያለው ሕዝባችን አካል እንደመሆናቸው መጠን ጨቋኝ ስርዓቶችን ለመጣል በተደረገው እልህ አስጨራሽ ትግል የበኩላቸውን ሚና እንደተጫወቱ ሁሉ በትግሉ የተጐናፀፍነውን ሕገ-መንግስት መጠበቅ እንዳለባቸው ጠቅሰው ለቀጣዩ ትግል ጥሪአቸውን አቅርበዋል።

**የቀኑን ታላቅነት አስመልክቶ የተዘጋጀው ኬክ በክብርት አምባሳደር ብርቱካን አያኖ መሪነት በብሔሮች፣ ብሔረሰቦች ተወካዮች ሲቆረስ፣**



**ኦታዋ**



**ቶሮንቶ**

በመቀጠልም "ዴሞክራሲያዊ ብሔርተኝነት እና የሕብረ-ብሔራዊነት ግንባታ ሂደት በኢትዮጵያ ፌዴራል ስርዓት" በሚል ርዕስ ላይ ገለፃ ቀርቦ በበዓሉ ታዳሚዎች ውይይት ተደርጐበታል። በተደረገው ውይይትም ሕብረ ብሔራዊነት በዲሞክራሲያዊ ብሔርተኝነት አመለካከት አስከተመራ ድረስ ፀጋ እንጂ የችግር ምንጭ እንዳልሆነ ለዚህ ደግሞ ከኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካ ኢኮኖሚ የሚመነጩትን የብሔር ትምክህተኝነትና የጠባብ ብሔርተኝነት አመለካከቶችን መሠረታቸው እስኪጠፋ ድረስ መታገል እንደሚገባ ከመግባባት ተደርሷል።

**ዴሞክራሲያዊ ብሔርተኝነት እና የህብረ ብሔራዊነት ግንባታ ሂደት በኢትዮጵያ ፌዴራል ስርዓት በሚል ርዕስ ውይይት ሲደረግ፣**



**አታዋ**



ከዚህ በማስከተልም በሁለቱም ከተሞች በተከበረው በዓል በየከተሞቹ የሚኖሩ የአገራችን ብሔረሰቦች ተወካዮች የቀኑን ታላቅነት ገልጸው ሕገ-መንግስቱን የመጠበቅ አስፈላጊነት ላይ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

**የብሔር ብሔረሰቦች ተወካዮች በበዓሉ ላይ መልዕክት ሲያስተላልፉ፣**



**ኦታዋ**



ቶሮንቶ

በመጨረሻም በበዓሉ ላይ የተገኙት ታዳሚዎች በአገራችን ብሔር ብሔረሰቦች ሙዚቃ ሲዝናኑ አምሽተል።